# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)

## Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org     E-mail: hq-office@moreshwegenie.org


ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

September 9, 2020

### ለውድ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ፥

**የኢትዮጵያ 2013 አዲስ ዓመት የመልካም ምኞት መግለጫ፤ እንኳን ለእንቁጣጣሽ አውደዓመት በሰላም አደረሳችሁ!!!**

በሞረሽ ወገኔ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በራሴ ስም መጪው **የኢትዮጵያ 2013 አዲስ ዓመት** የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የመተሳሰብ፣ የብልጽግና፣ የደስታ፣ በተለይም የጤና እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞታችንን እየገለጽን፤ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያም ለልጆቿ አንድነትንና ትብብርን ሰጥቶ፣ ከቤታቸው ወጥተው በሰላም የሚገቡበት፣ ከቤት ንብረታቸው ተገፍተው የወጡ እንዲሁም በማንነታቸውና በእምነታቸው ተለይተው የተፈጁ ፍትህ የሚያገኙበት፣ ያዘኑ የሚጽናኑበት፣ የተራቡ የሚመገቡበት፣ የታመሙ ፈውስን የሚያገኙበት ጊዜ እግዚአብሔር ያሰፍንልን ዘንድ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን።

በተለይ በሲቪክ ድርጅትነት ሞረሽ ከቆመለት ራዕይ አንጻር፥ በኢትዮጵያ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን  በሙሉ በሀገራችሁ የትኛውም ጥግ ተዘዋውራችሁ የመሥራት፣ የመበልጸግ፣ ቤተሰብ የመመስረትና፣ በሰላም የመኖር መብታቸችሁ ይከበር ዘንድ በአንድነት እንድትቆሙ፤ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሌላው ኢትዮጵያዊ ጠባቂ መሆኑን  በማሰብና ነባር እሴቶቻችሁን ተጠቅማችሁ ሁላችሁም የወገን አለኝታና መከታ በመሆን ይህን ክፉ ጊዜ ቶሎ ታሳልፉት ዘንድ የእግዚአብሔር ፍቃዱ እንዲሆን ልባዊ ምኞታችን ነው።

መጪው 2013 የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከገባችበት አጣብቂኝ የምትወጣበት፤ መላው ዜጎቿ መሰረታዊ ሰብአዊ መብታቸው የሚከበርባት፣ በሰላም ከቤታቸው ወጥተው የሚመለሱባት፣ ፍትህ የሚያገኙበት፣ ለእኩልነትና ዲሞክራሲ የሚያደርጉት ትግል ፍሬ የሚያፈራበት፣ እንዲሁም በ2012 ተከስቶ፣ ዓለምን ያስጨነቀው የወረርሽ በሽታ ድባብ ተገፎ፤ በወገናችን ላይ ያሳረፈው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ህይወት ጫና የሚቃለልበት ዘመን እንዲሆን የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

በድጋሚ መልካም የ2013 አዲስ ዓመት ይሁንላችሁ!!!

ከአክብሮት ጋር

አረጋኸን ንጋቱ (ዶ/ር)
የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ሊቀመንበር